የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

No 2289/1205
Date 17/3/2015

ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ፤

የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ የተላለፈ ጥብቅ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

*የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ ፤ ወደ ድሀ አደጎች እርሻ አትግባ ፤ ታዳጊአቸው ጽኑ ነውና ፥ እርሱም ፍርዳቸውን ከአንተ ጋር ይፋረዳልና ። ምሳሌ 23 ፥ 10-11 ።*

ምንም እንኳ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያን በግፍ እየገዛ ያለው የሽፍታ መንግሥት ፥ ግፍ ከመፈጸም ያቆመበት ጊዜ ባይኖርም ፣ አሁን ግን አገርን አሳልፎ ከመሸጥ ጀምሮ ፥ ያለማቋረጥ እያካሄደ ያለውን ግፍ በቃላት ከመግለጥ በላይ ሁኖ አግኝተነዋል ። ስለ ሆነም ቅዱስ ሲኖዶስ ፣ ይህን ምን አልባትም የመጨረሻ የቤተ ክርስቲያን ታላቅ መልእክት በውግዘት ለማስተላለፍ ተገዷል ።

ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ፥ አስተውሎ ለሚመለከተው የሰው ልጅ ሁሉ ትልቅ ትምህርት ነው ። ከአንባ ገነኑ የወያኔ መንግሥት በስተቀር ፣ የየትኛውም አገር መንግሥትና ሕዝብ ፥ከአባቶቹ የተረከባትን ሀገር ከመጠብቅም አልፎ ይሞትልታል ። ማንኛውም መንግሥት ዜጎችን እንደ አባት ሁኖ ሲመራና አገርንም እንደ ዘበኛ ሁኖ ሲጠብቅ በየትኛው አገር ይታወቃል ። አንባ ገነኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ፥ እነዚህን የመንግሥትነትን ባሕርይ የሚያሳዩ መርሆዎችን በሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ ፈጽሞ ማሳየት አልቻለም ። የአገሪቱን ድንበር አሳልፎ ሲሸጥ በቦታው የሚኖሩ ኢትዮጵያውን ዜጎች በሙሉ የት ቦታ እንደሚኖሩ ፥ በምትኩ ምን እንደሚሰጣቸው ፥ የዜግነት መብታቸው የት ድረስ እንደ ሆነ ፤ ለዚህ አንባ ገነን መንግሥት ጉዳዩ አይደለም ። በሀገሪቱ በየትኛውም ቦታ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቦታቸው እየተቀማ ለውጭ አገር ነጋዴዎች እየተሰጠ ፥ የሀገሪቱ ዜጋ ከትውልድ አገሩና መንደሩ ተነቅሎ ስደተኛ ሲሆን ፣ ይሄ አረመኔ መንግሥት ፈጽሞ የሚራራበት ልብ የለውም ።

ይህ ደግሞ በሰውም በታሪክም በእግዚአብሔርም የሚያስጠይቅ ነው ። ቃሉ እንደሚለው "ወደ ድሀ አደጎች እርሻ ማለት እርስት አትግባ አትውሰድ ፥ ታዳጊያቸው ጽኑእ ነውና እርሱም **ፍርዳቸውን** ከአንተ ጋር ይፋረዳልና" ስለሚል ፣ የራሱን ዜጎች ተወልደው ያደጉበትንና የሚኖሩበትን ቦታ ቀምቶ ለባዕድ መንግሥት ሰጥቶ ሕዝቦቹን የት ወደቃችሁ የማይል ፣ የራሱን ሕዝብ በባዕድ ወታደር እንዲገደሉ የሚያደርግ መንግሥት ፥ መንግሥት ተብሎ ሊጠራ አይችልም ። ይህ ድርጊት በየትኛውም መለኪያ ቢሆን ወራሪ ኃይል እንኳ የወረረው አገር ዜጋ ጦር ካላነሣበት በቀር ፣ በኃይል የያዘውን አገር ቀምቶ ለሌላ መንግሥት ሲሰጥ ታይቶም ተሰምቶም

አይታወቅም ። እስከ አሁንም አልሆነም ፥ ወደ ፊትም አይሆንም። ይህንን የሚያደርግ መንግሥት ፥ መንግሥት ብሎ ለመጥራት አንደበት ፈቃደኛ አይሆንም ።

በሌላ መልኩ የኦሮሞ ማኅበረሰብ የሚኖሩበት መኖሪያ ቤታቸውንና አርሰው የሚጠቀሙበትን መሬታቸውን በልማት ስም አትቀሙን በማለታቸውና ይህን የዜግነትና ሰብዓዊ መብታቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲከበር የጠየቁትን ዜጎች የጦር መሣሪያ በታጠቀ ኃይል የሚያስገድል ፣ ካልታደለችው ከኢትዮጵያ ጨካኝ መንግሥት በስተቀር ሌላ መንግሥት በዓለም ተፈልጎ አይገኝም ።

ይህ እጅግ በጣም የተጠላ አንባገነን የወያኔ መንግሥት ፣ የራሱን ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲጋደል መሣሪያ የሚያስታጥቅ ፣ አንዱ ወገን በሌላው ላይ ተነሥቶ እንዲገድለው የሚያሠለጥን ፣ የነፍሰ ገዳይነት ሥልጠና የሚያካሂድ ፣ ባለፉት ዓመታት እንደ ተደረሰበት የራሱን ሕዝብ በተጠመደ ፈንጅ ገድሎ ፥ በሌሎች እያመካኘ የሚያስር ፣ በየትኛው መለኪያ [illegible]

አድራጎታችሁ እንድትቀጠቡ ፣ በግፍ በሚገደሉት ፥ በእስር ቤት በሚሰቃዩትና በሚሰደዱት ወገኖቻችን ስም ከታላቅ አደራ ጋር ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል ።

3). ይህ መንግሥት ተብየ ቡድን ለግለሰቦች ጥቅም ሲል የሀገራችን የተፈጥሮ መልክአ ምድራዊ ሥርዓትን በማፋለስ ፣ ለም ቦታዎችን ለሱዳን መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት በሚያደርገው ክፉ ሴራ ፥ ተባባሪ የሆናችሁ ፣ በየትኛውም ቦታ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ወግገኖቻችን በሙሉ ለዚህ ክፉ ሥራ ተባባሪ ሁናችሁ የታሪክ ተጠያቂ እንዳትሆኑ አሁኑኑ ይህን ክፉ አድራጎት እንድትቃወሙ ፣ ከአደጋ ቀይ መብራት ላይ ባለው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ስም ፣ ታሪካዊ የአደጋ ጥሪ ደወል እናሰማለን ።

4). የቅማንት ማኅበረሰብ ወገናችን ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሕዝባችሁ መካከል ይህ ክፉ መንፈስ የተጠናወተው መንግሥት የሚሰጣችሁን የውሸት ፕሮፓጋንዳ እንደ እውነት ቈጥራችሁት ከሆነ ፣ ይህ አይነቱ መንፈስ ለወያኔ ካልሆነ በቀር ለጠቅላላው ሕዝብ ስለማይጠቅም ፣ ከዚህ ራስን ከማጥፋት ድርጊት እንድትቀጠቡ ከታላቅ አደራ ጋር ጥሪያችንን እያስተላለፍን ፣ ይህ ድርጊት የወያኔ መንግሥት ሥራ እንጂ የኢትዮጵያውያን ስላልሆነ ይህን አውቆ ሕዝቡ ከዚህ አድራጎት እንዲቀጠብ አደራችን እናስተላልፋለን ።

5). ለኢትዮጵያውያን የትኛውም እምነት ተከታዮች በሙሉ ፣ ይህ ጊዜ ከመቸውም ጊዜ በላይ በአንድነት ሁነን በጸሎት የምንተባበርበት ጊዜ ነው ። ሕዝባችን የረኃብ ፥ የጦርነት፥ የስደት ተጠቂ ሁኖ በዓለም መዘባበቻ ሁኖ ይታያል ። በዚህ ጊዜ ነው በአንድ ልብ ሁነን ወደ ፈጣሪ በንስሐና በጸሎት መቅረብ የሚኖርብን ። ይህን ቸል ብለን ሕዝባችን እያለቀ ዝም በማለት የታሪክ ተጠያቂ እንዳንሆን ዛሬውኑ ይህ የመከራ ዘመን እንዲያበቃ የእግዚአብሔርን ምሕረት እንድንለምን ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንኦት ጥሪ ያቀርባል ።

6). በመጨረሻም የሰማይ አምላክ ይህን ሁሉ መከራ እንደሚያሳልፈው በማመን ሁሉም ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ እየጸለየ በርሐብ አለንጋ እይተገረፈ ላለው ሕዝባችን መላ ኢትዮጵያትውያን በግልም በማሕበርም ተደራጅቶ የዕለት እርዳታ ከማቅረብጋር እንዴተበብር እየጠየቅን በሌላ መልኩ ግን በምንም መንገድ ይህ መንግሥት ለሚያስተላልፈው የጥፋት ሥራ እንዳይተባበር በእግዚእብሐር ስም ጥሪ በማቅረብ ፣ ለሁሉ መፍትሔ ሰጭ አምላክ ስለ ሆነ ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጸሎት እየተጋ ፥ ለሰላምና ለይቅርታ እንዲሠራ በወገኖቻችን ስም ጥሪ እናስተላልፋልለን ።

ልዑል እግዚአብሔር ለውድ አገራችን ለኢትዮጵያ ሰላምን ፥ ለሕዝባችንም አንድነትን ፥ ይስጥልን ፤ አሜን ።

አባ መልከ ጼዴቅ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ

አባ መልከጼዴቅ ካህኑ ለእግዚአብሔር
ABBA MELKESEDEK ARCHBISHOP